# በሴቶች ላይ በደል መብዛቱ፤ የስርዓቱ መገልማቱ

ወይኒት ሞገስ

- ሰምንት ወጣት ሴቶች በአረብ ሀገር በመርዝ ተገድለው ተገኙ፤
- በሳምንት አንድ ኢትዮጵያዊ ሴት በሌባኖን ትገደላለች ወይም ትሞታለች ተባለ ፤
- በኩፍራና ሌሎች የሊቢያ እስር ቤቶች ብዙ ወጣት የሀገራችን ሴቶች ግፍ እየደረሰባቸው ና ለሞትም እየተዳረጉ ነው፤
- ወደ የመን ሲጓዙ ከሚሞቱት ስደተኞች ውስጥ ብዙዎቹ የኢትዮጵያ ሴቶች ናቸው፤
- በኢትዮጵያ ምድር ለሴትኛ አዳሪነት የሚዳረጉት ሴቶች ዕድሜ ወደ 11 በነፍስ ወከፍ ወረደ ተባለ፤
    - ወጣት ሴቶችን ለዘመናዊ ባርነትና ለሴትኛ አዳሪነት መማገዱ እየተስፋፋ ሄዷል::

የኢትዮቻነል ጋዜጣ ጋዜጣ ቅጻሜ ሐምሌ 4 ባወጣው ዕትሙ ደግሞ በአባቷ ተደፍራ የነበረችው የ13 ዓመት ወጣት ከሪማ በአባቷ ላይ ክስ ከመሰረተች በኋላ ራሷን መስቀሏንና መግደሏን አትቶ ደፋሪው አባቷም አቶ ሰይድ አባገሮ በ25 ዓመት ፅኑ እስራት እንደተቀጣም አትቷል:: ባለፈው ሰሞን ደግሞ ልጁን ከውሻው ጋር አስሮ ሲደፍራት የከረመን አባት ጉድ አንበናል:: ምን እየሆንን ነው? ወያኔ እንደሚለው ድሮም ያለና የተደበቀ ዛሬ ግን ዕድሜ ለወያኔ ይፋ ወጥቶ አጥፊው እየተቀጣ ነው? ሕብረተሰቡ የነበረው ጨዋነትና የስነ ምግባር ህግ የት ደረሰ ? ወይስ ይህም የምዕራቡ ካፒታሊዝም ስርዓት የማይቀር ዝቅጠትና መዘዝ ነው?

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ የብዙ ጎጂ ባህሎች ሰለባ መሆኑ የሚታወቅ ነው:: በርግጥ ይኸ መነሳቱ ገበናን ማስጣት ነው ብለው ለምን ተወስቶ የሚሉ አሉ:: ሕዝብ ተራብ እርዱን ሲባል ተዋረድን የሚሉት ቅምጥሎች ዓይነት ናቸው:: ህቁ ሲነገር  የሚያማቸው ካሉ ችግሩ የራሳቸ ው ነው:: በሀገራችን ግን በተለይ ሴቶችን የሚጎዱ ባህሎች መሰንበታቸው የሚካድ ጉዳይ አይደለም:: ትልቁ የአፍሪካ የፌስቱላ  ህክምና ቤት/ሆስፒታል በአዲስ አበባ መገኘቱ በአጋጣ ሚ አይደለም::  ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ ሴቶችን መዳር የቆየ ነው:: የነበረንን ያለንን አመለከካት እስቲ በጥቅሶቻች አማካይነት እንጎብኛቸው፤---

- ሴት በዛ ጎመን ጠነዛ
- ሴት ታውቅ በወንድ ያልቅ
- ሴትና ዶሮ ጲር ከሄዱ ቤታቸውን ይከዱ
- የሴትና የገንቦ ትንሽ የለውም
- ሴትን ከቤት ብርን ከማድቤት

- ሴትን ያመነ ጉምን የዘገነ
- ሴት ማገዶ ቢቸግራት ምሰሶ ትነቅላለች
- ሴት ለቤት ወፍጮ ለዱቄት
- ሴትና በቅሎ እንደ ገሪዋ ነው
- ሴት አግብተው ሴት ቢወልዱ የት አለ ንግዱ
- ሴትና ፈረስ ያቀረቡለትን ይቀምስ
- ሴትና አህያ ዱላ ካልቀመሱ ቦታቸውን ይረሱ
- ወዘተ ወዘተ

በየብሄረሰቡ ያሉ ባህሎች ከሞላ ጎደል ለሴቶች መብት ተፃራሪ ናቸው ቢባል ስህተት አይሆንም፡፡ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች ቦታዎች በሀይማኖት ሽፋን ሴቶችን መበደልና በዝቀተኝነት ደረጃ መጫኑ ተስፋፍቷል፡፡ ሁሉም ሰው ሊያውቅ እንደሚገባው በደፈናው ባሕል ትበሎ ሁሉም ባህል በጎና ጥሩ ሊባል አይችልም፡፡ መንገኛ ላይ አድብቶ ቆይቶ ገድሎ መስለብ ባህላችን ነው ስለተባለ በርቱበት የሚባል አይደለም፡፡ ሴት አግብቶ ፈቶ ወንዱ ሌላ ሲያገባ የተፈታችው ሚስት ማንንም እንዳታገባ መከልከሏ፣ ሴት ማመር የለባትም መባሉ፣ወዘተ  ባህል ተብሎ ሊቆይ የሚፈቀድለት ሊሆን አይችልም፡፡ ባሏ ሲሞት ሚሰትየዋን ወንድሙ ማግባቱ መቆም ያለበት ባህል ነው፡፡ በእህት ልዋጭ ሚስት ማግባት፣ በ10 ዓመት ህፃኒቷን መዳር፣ ሚስትን ነጋ ጠባ መደብደብ፣ የሴት ልጅን ሰውነት መቆራረጥ፣ በባርነት ደረጃ መያዝ፣ ሴትን በማንአለብኝነት መድፈር፣ ወዘተ ሊከለከሉና ለቅጣትም ሊያደርሱ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ በዚህ ዙሪያ ምንም ለቀቅተኝነት እንዲኖር መፈቀድ የለበትም፡፡

ወደ ተነሳንበት ዋና ርዕስ ስንመለስ ግን በአሁኑ ጊዜ ተስፋፍቶ የሚታየው የሞራል ዝቅጠትና የተባባሰው የሴቶችን መብት ረገጣ  በመሰረቱ የገለማው ሥርዓት ውጤት መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ የሞራል አጥር ሲነቀልና ለከትና ይሉኝታ ሲወድሙ የመጀመሪያ ተጠቂዎች ሴቶችና ህፃናት ናቸው፡፡ ሰው ወደ እንስሳነት ሲንሸራተት፣ ሆዱና ስሜቱ ሲገዛው ተጠቂዎች ሴቶችና ህፃናት ናቸው፡፡ የእኛው ቢቀር የምስራቅ ኮንጎን አረመኔ ሚሊሺያ ፀረ ሴት ድርጊቶች ያጤኗል፡፡ የሰው ልጅ በአስተዳደጉ፣ በህብረተሰቡ፣ በባህልና ቅርሱ የተነሳ ስነ ምግባርን ይዞ በስርዓት የሚኖርበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ይህ ባልሆነበት ደግሞ የሰው በላ ስርዓት ጫና ሰለባ ይሆንና መረን ለቀ ወገኑን ያጠቃል፣ ልጁን ይደፍራል፣ ልጁን ለዘመናዊ ባርነት ይሸጣል፣ እርስ በርሱም ይናከሳል፡፡ በኢትዮጵያ የመብት ረገጣ ሁኔታ ለዘመናት የቆየ ቢሆንም ዛሬ የሚታየው የህብረተሰቡ የሞራል ግንብ መፍረስና የሴቶች የተባባሰ በደል መከሰት የወያኔ ስርዓት ውጤት ነው፡፡ የወያኔ መሪዎች እናት ሀገራቸውን የከዱ ብቻ ሳይሆኑ እናታቸውንም እህቶቻቻውንም ያላከበሩ ናቸውና አገዛዛቸው ዝቅጠትን ክቡር አድርጎ ያቀረበ ነው፡፡ የሴቶችን መብት ሊያስከብሩ ቀርቶ የወያኔ ዋና ባለስልጣኖች ወጣት ሴቶችን የሚደፍሩና የሚያባልጉ መሆናቸው ዛሬም ቀጥሎ እየታየ ያለ ሀቅ ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስቴር ነኝ የሚለው ሰው ራሱ በየተሲዓቱ ፈርሾ ጫት ሲቅም አርአያነቱ ምን

መሆኑ ግልፅ ነው:: ባለጌውና ሰካራሙ ስብሐት ነጋ በስተርጅና የ20 ዓመት ወጣት ልጅ መወሽ ሙን ሕዝብ እያወቀ የዚህ መልዕክቱ ለማንም ስውር አይደለም:: ጡት ራቁት የ 15 ዓመት ሴት ልጆች ዊስኪ አቅራቢ በሆኑበት መጠጥ ቤት እነ ፕሮፌሰር እንድርያስ እሸቴና ሌሎች ስም አይጠሬ ባለጌዎች ከነ ሀሺሻቸው መያዛቸው ሌላ ምሳሌ ነው:: አቡን የተባሉትም ባልገዋል:: የገዢው ክፍል አባል የሆኑት ህፃናት ሴቶችን ይደፍራሉ:: ሴት ይለዋወጣሉ:: ምንም ስነ ምግባር ና ስነ ስርዓት የላቸውም:: ስርዓታቸውም በሙስናና ግለኝነት፣ስግብግብነትና ልክስክስነት የተዋጠ በመሆኑ ለአዳጊው ትውልድ መርዝ መርጨቱ አልቀረም:: ይህ ደግሞ ሳያስቡት ሳይሆን አውቀ ው የሚያደርጉት ነው:: ትምክህትና ብልግናን ሲያነግሱ በዚያው ሴቶችን መናቁና ማዋረዱ ይከተላል:: ሰዉም የሞራል አጥሩና ግድቡ ይፈርሰበትና ለተራ ስሜቱ ተገዢ ሆኖ በደል ይፈፅማ ል:: የወያኔ ስርዓት በባህል መስክም በሕዝብ ላይ ሰፊ ጥቃት እያደረሰ በመሆኑ በተለይ ወጣቶች ን በጠባብ ትምክህት ብቻ ሳይሆን በጫቱም፣ በአልኮሉም፣ በአደንዛዥ ዕፁም ወዘተ በክሎ ና አዳክሞ ሊገዛ ዘመቻውን ቀጥሏል:: የባልሥልጣኖቹ ልጆች ቢሆኑም የዚህ ዝቅጠት ዋና አንፀባራ ቂ ሆነው ይገኛሉ:: በዚህ ሁኔታ ሴቶች መጫወቻ ተብለው መወሰዳቸው የሚያስገርም አይሆንም :: እገሊት እገሊት ተብሎ አንዳንዴ ስም ቢነሳም በፖለቲካው ዓለምም ቢሆን ሴት ታውቅ በወንድ ያልቅ አሁንም ሰፍኖ ያለ ነው::

አባቷ በእስራት ስለተቀጣ የከሪማ ህይወት አይመለስም ግን ሴቶችን የሚደፍሩ መቀጣታቸው አስፈላጊ ነው:: የሀገሪቷ የወንጀለኛ መቅጫ ና የቤተሰብ ህግ በሚገባ የሴቶችን መብት እያስከበሩ አለመሆናቸው ይታወቃል:: ለሁሉም ዋናው ተጠያቂ ግን የሕዝብን የሞራልና ስነ ምግባር ህግና ቅርስ ያጠፋው ነው:: በሀገራችን ዝቅጠትና ብልግና እየተስፋፋ ያለው በወያኔ አገዛዝ ነው:: አሳው ከጭንቅላቱ መግማቱ ህብረተሰቡን አቆሽሾታል:: ትላንት ያልነበሩ ወይም ተስፋፍተው ያልነበሩ አልባሌ ጠባዮች ዛሬ ተስፋፍተዋል:: ጎጂ ባህሎች ነበሩ ቢባልም ዛሬ ወያኔ ባመጣቸው በበርከታ ቆሻሻ ልምዶች ታጅበው ዳብረዋል:: በአንድ ሀገርደ ስሞክራሲ መስፈኑን መመዘኛ የሴቶች መብት መከበር አለመከበር ነው ተብሏል:: የወያኔ አገዛዝ ፀረ ዴሞክራሲነት በተለይ ሴቶች በሚኖሩበት አስከፊ ሁኔታ የሚጋለጥ ነው:: ያልተለመዱ ፀረ ሴት ፀረ ህፃን ብልግናዎች መከሰታቸውም ምክንያቱ ይኸው አገዛዝ በድህነትና በቀቢፀ ተስፋ የተጠቃውን ዜጋ በአልባሌ ባህሎችና ልምዶች --በተለይም በከተሞችና በወጣቶች ዘንድ--በመበከሉ መሆኑ ግልፅ ነው:: በባዕድ ሀገር ነዋሪ የሆኑ ዜጎችም ወደ ኢትዮጵያ እየሄዱ በዚሁ የዘቀጠ ብልግና ተካፋይ በመሆን ህፃናትንም ጭምር እየጎዱ መሆናቸው መጠቀስ የሚገባው ነው::

የኢትዮጵያ ሴቶች ለመብታቸው መከበር ብዙ መስዋዕተነትን ከፍለዋል:: የአድዋ ጦርነተ ድል ለወንዶች ቢሰጥም የድሉ ማገርና ምሰሶ ሴቶች ነበሩ:: ፋሺት ወራሪውንም ሴቅተች ጠመንጃ ይዘው ሆነ የትግሉ ጀርባ አጥንት ሆነው ታግለዋል:: በየካቲት አብዮት ሴቶች መብታቸውን

ለማስከበር መሰለፍ ብቻ ሳይሆን በፀረ ደርጉ ትግል ግንባር ቀደም ሆነው ወጣት አሮጊቷ ሁሉም አስተዋፅዖ አድርገዋል። ብረት ይዘውም ታግለው ጠላትን ዋጋውን ሰጥተውታል። ወያኔን ሲታገሉ የተሰዉ ጀግና ሴቶች፣ ተይዘው ደብዛቸው የጠፋ እነ አበራሽ በርታና ሌሎችም የሚጠቀሱ ናቸው። በ 1997ኡም ፍጅት አያሌ ሴቶች የሕይወት ዋጋ ከፍለዋል። መብታቸው ሊከበር አለመቻሉ ትግል ባለማካሄዳቸው ሳይሆን ያው በሁሉም ሕዝብ ላይ የመጣው የአምባገነን መዓት የበላይነትን ስለያዘ ነው። ሴቶችም ከመቸውም ጊዜ በከፋ እየተበደሉ ያሉበትን ሁኔታ የኢትዮጵያ ሕዝብ የቆየ ባህል ነው ብሎ ማስረዳት የሚቻልም አይደለም። የአሁኑ መከራ ና ዝቅጠት የወያኔ አገዛዝ መራራ ፍሬ ነው። ለዚህም ነው ይህንን ጨቋኝ አገዛዝ ለማስወገድ የጋራ ትግሉ መፋፋም ያለበት። የጋራ ስንልም የሴቶችን የራሳቸውን የመደረጃት መብት በመፃረር ወይም በመሰረዝ ሊሆን አይቸልም። ሴቶች በራሳቸው እንደ ሴት ተደራጅተው ለመብታቸው መታገላቸው ቅንጦት ሳይሆን የትግላችን ድልና የዴሞክራሲ መረጋጋጥ ዋስትና ነው።

ለሴቶች መብት መከበር እንታገል!!
የኢትዮጵያ ሕዝብ በወያኔ ላይ ድልን ይቀዳጃል!!